በተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶች ህብረት በጃፈርሰን መታሰቢያ ሀውልት ላይ፡ መስከረም 15 ቀን በተደረገው ጉባዔ ላይ ከቀሲስ አስተርአየ የቀረበ ነው።

# እንባችን ተሟጧል

## በኢትዮጵያ እና በዓለም ዙሪያ በሩቁ ያላችሁና በፊታችሁ ቆሜ የምታዩኝ

ቤተ እስራኤሎች፡-

ክርስቲያኖች፡-

ሙስሊሞች፡-

ሁላችንም የምንስማማበትን በሙስሊሙ አባባል ዘቡር በሚባለው በዳዊት መጽሐፍ የተመዝግበውን በውስጥ ከሚሰቃየው ወገናችን ጋራ በመተባበር "ተካውኩ ከመ ማይ ወተዘርዎ ኩሎ አዕጽምትየ ወኮነ ልብየ ከመ ሰም ሰይትመሰው በማእከለ ከርስየ" (መዝሙር 22፡ ) ለማለት በዚህ ቦታ ተሰብሰበናል። ይህም "መላ ሰውነቴ ወደ ውሀነት ተለውጦ ተደፋ። አጥንቴም ደቅቆ ወደ አፈር ትቢያነት ተለውጦ ተበታተነ። ልቤም እንደሰም ቀልጣ በአንጀቴ ፈሰሰች" ማለት ነው።

ወደ ውሀነት ተለውጦ ወደ መሬት ከተደፋ ሰውነት እንባ አይታሰብም። ወደ ትቢያነት ተለውጦ ከተበተነ አጥንትም ቁመተ ሥጋ የለም። እንደ ሰም ቀልጦ በአንጀት ከፈሰሰች ልብ በሰውነት የሚሰራጭ ደም የለም። ኢትዮጵያውያን ሁላችንም ከዚህ ላይ ደርሰናል። ይህን አሰቃቂ የዘር ማጥፋት እስከ ህልፈተ ዓለም የማይረሳውን ታሪክ ወያኔዎች ገና ሲመሰረቱ ባማራው ጀመሩት። በኦሮሞው ላያ ቀጠሉ፤ በየጠረፉ ባሉት ኢትዮጵያውያን ጎሳዎች ሁሉ ላይ ፈጸሙት።

ይህን ግፍና መከራ በእግዚአብሔር ቃል በመለካት መወገዝ እንዳለበት ከኔ በፊት ምስክርነታቸውንና ወገናዊ ስሜታቸውን የገለጹት ወገኖቼ ተናግረውታል።

እኔ መናገር የፈለጉት፤ ኢትዮጵያ አገራችንን ያለችበትን ወቅታዊ ሁኔታ ስለሚያሳይና የዕለቱም በዓል ስለሆነ የደመራ በዓል ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን በያመቱ እንዲታወስ ለምን እንዳደረገችና ለትግራይ አዛውንቶች ካህናትና ሊቃውንትም የሚመለከት ተገቢ ታሪካዊውን መልእክት ስላለው ላቀርብላቸው ስለፈለኩ ነው።

የደመራን ይዘትና አላማ ከዚህ ቀደም ደመራ በሚል ርእስ ስለቀረበ አሁንም በመነበብ ላይ ስላለ ወደ ውስጥ አለገባም። ምዕራባውያን liberal theology ብለው ለነጻነትና ለሰው ልጅ ከመንቀሳቀሳቸው በፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በዓላትን ለኢትዮጵያውያን ክብርና ልዕልና ለዳር ድንበር መጠበቂያ ምሽጎች አድርገው ሰርተዋቸዋል። ደመራም ከነዚህ ምሽጎች አንዱ ነው።

# <u>ደመራ ከመከላከያ ምሽጎች አንዱ ነው</u>

አባቶቻችን በመጽሐፈ መሳፍንት ምዕ ፱ ከቁጥር ፳ ላይ የተመዘገበውን ። “ለትጻዕ እሳት እምቤተ አቤሜሌክ፥ ከመ ትብላእ አብያተ ሴኬም፡ ወትሜሎም:: ወለእመ አኮ እሳት ትጻእ እምቤተ ሴኬም ወትሜሎም ከመ ትብላዕ ቤተ አቤሜሌክ” የሚለውን ንባብ ለነጻነት ተጠቅመዋል።

ፖርቹጋሎች በእርዳታ ስም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው አንወጣም ብለው ኢትዮጵያን በወረሩ ጊዜ ኢትዮጵያውያን በወራሪዎች እየተሰቃየን ለዘላለም ከመኖርና ለልጆቻችንም የተገዥነትን ውርስ ከማውረስ ይሕች ከየቤታችን የጫርናት የችቦ እሳት ትብላቸው” ብለው የደመራውን እሳት በመጠቀም የፖርቱጋሎችን ቤትና ንብረት በማቃጠል ነጻ ወጡበት።

ለደመራው በዓል መነሻዋ እሌኒ ብትሆንም፥ መምህራን ሲነጋገሩ እንደሰማሁት፥ እሌኒ ደመራ ብላ አልሰየመችውም:: በዓሉ ደመራ ተብሎ አሁን በምናከብረው ሁኔታና መንፈስ በአገራችን ከመከበሩ በፊት፥ የመስቀል በዓል እየተባለ ነበር። በደመራው ዙሪያ የሚካሄደው የካህናቱ ቃል የወጣቱ እንቅስቃሴ አርባኛነትን ብሄርዊ ክብርንና የአገር ሉአላዊነት የሚያንጸባርቅ ነው።

አባቶቻችን ቆርጠው ተነስተው ነጻነታቸውን ያገኙበትን ለማስታወስ ፤ የሚመጣውም ትውልድ ያለፈውን እንዳይረሳና ዘመኑ በሚጠይቀው ዘዴ ለነጻነቱ እንዲጠቀምበት በያመቱ እንዲከበር አደረጉ። በዓሉም በአርበኞች አዛውንቶች፤ እናቶችና በወታደራዊ ትእይንት በግርማና በሞገስ እየታጀበ ይታወስ ነበር።

ወያኔ ለ25 አመታት ይህንን የአርባኛነት ውርስ ደምስሶና ወጣቱ እንዲረሳው ካደረገ በኋላ ። እራሱን እንዳይመክት ለወደፊቱም ኢትዮጵያን የሚረከብ ትውልድ እንዳይነሳ የአማራው የኦሮሞውና የአፈሩ የቀረው ጎሳ ሁሉ ዘር እንዳይቀጥል ሁሉንም ደርቦ መጨፍጨፉን ቀጠለ ።

ወያኔ በክፋትና በቂም በተበከለው ህሊና እየተቃኘ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የፈጸመው ግፍና ያረመኔነት ተግባር ፤ በዕድሜ ብቻ ከሚበልጠው ሰይጣን ከሚፈጽመው ጭካኔ ጋራ እንኳ የማይነጻጸር መለኪያ የሌለው ነው።

የወያኔዎችን ጭካኔ ንጽጽር የሌለው የሚያደርገውም፤ ክርስቶስ "ሰይጣን ሌላውን ሰይጣን አያስወጣውም" (ማቴ 12፡ 26) እንዳለው፤ ወያኔዎች የአርበኛነትን ትርጉምና መንፈስ ቀይረው፤ ከራሳቸው አራዊታዊ አስተሳሰብ በእጅግ የላቀውን ወገን፤ ታራሚ ነፍጠኛ እያሉ የሚፈጽሙትን ግፍና ጭካኔ ሰይጣን በሰይጣን ላይ ስለማያደርገው ነው።

ይልቁንም ትክክል አይደላችሁም የሚሉትን ሁሉ አዛውንቶችን እናቶችን ጸሀፊዎችን ታራሚ እያሉ አሰሩ አሳደዱ ገደሉ። ለሰባዊ ልዕልና የቆመችውን ቤተ ክርስቲያንና ክርስቲያኑን ከሰበሩ በኋላ፤ የሚናገሩትን ክፋት የተሞላ ሸፍጥ የሚደብቁላቸውን፤ የሚናገሩላቸውንና የሚያስተጋቡላቸውን፤ የሚፈጽሙትን ድብደባ ግድያ እስራትና እንግለት ለማረም እያሉ እያደነቁና እያሞካሹ ለዓለም የሚያቀርቡላቸውን ጳጳሳት ካህናት ቆሞሳት ሰባክያን አዘጋጁ።

ወያኔዎች ኢትዮጵያን ከተቆጣጠሩ በኋላ ከዚህ በታች የምጠቅሳትን ታሪካዊት ትዝታ ቀይረው ለወጣቱ ለማቅረብ ያደረጉት ጥረት እጅግ የሚገርም ነው።

በወያኔ ዘመን ከተወለዱ ወጣቶች በቀር፤ በያመቱ የሚከበረው የጥምቀትና የደመራ በዓል የሚደመደመው ሁሉም በሚያውቀው በኦሮሞውና በወያኔዎች መካከል በሚደረግ መቀጣቀጥ ነበር።

የጉራጌ ወጣቶች "ወያኔ ቴስታ እንጅ፤ እንደ ኦሮሞውና እንደ አማራው የዱላ ምከት አያውቅም። የሚያውቀው እንደ ፍየል በራሱ መዋጋት ነው። በሩቁ እጅእጁን በለው" እያሉ የባህርዛፍ ዱላ ከጉለሌ እየቆረጡ ለኦሮመው ያቀብሉ ነበር።

ወያኔ በበኩሉ "ኦሮሞዎችና አማሮች የጣሊያኖችን ቴስታ ስለማያውቁ ኦሮሞውንና አማራውን ግንባሩን በቴስታ በለው" እያሉ እስከ መጋደል ስለሚደርሱ የሚለያዩት በዓሉን በትእይንት ለማክበር በተሰለፈው ወታደር ኃይል ነበር ።

በያመቱ በሚደረገው በዓል ይህ በኦሮሞዎችና በወያኔዎች መካከል ያለው መደባደብ እንዴት ሊፈጠር ቻለ? ብለን ስንጠይቅ፤ ከሁሉም ሊቃውንት አበው የምንሰማው፤ "የትግራይ ባንዳዎች ወቅትና አጋጣሚ ሲያገኙ ባማራው ራስ ተረማምደው ኦሮሞዎችን ያጠቁ ስለነበረ ከዚያ የሚያመረቅዝ ቂም ነው" ይሉን ነበር።

ሊቃውንቱም እንደፍየል በቴስታ የሚዋጉትን የባንዳዎችን አሰላለፍ ከዚህ በታች የምጠቅሰውን በዳዊት መጽሐፍ ላይ ያለውን ሐረግ እየጠቀሱ፡-

“ቀርነ ኃይል ወቀርነ መድሀኒትነ ብከ ንወግኦሙ ለኩሎሙ ጸርነ” በሚለው በራሳቸው (በቴስታ) እንደ ፍየል የሚዋጉትን ወያኔዎችን እየፈረጁ፤

“ቀጥቅጥ መዝራእቶ ለኃጥእ ወእለኩይ” ”ወቀጥቀጠ አርዕስቲሁ ለለይሲ“በሚለው ኦሮሞዎችን በመፈረጅ ይቀኙበት ነበር።

ይህም ማለት፡- ወያኔዎች ኦሮሞዎችን እንደጠላት በመቁጠር ከግራዝያን በወረሱት ቴስታ የኦሮሞዎችን ራስ መተው በማዞር ያጠቃሉ።

ኦሮሞዎችና አማሮች የሚያውቁትና ያላቸው ልምድ፤ በረዠም ዱላ በሩቁ መመከት ነው። በምከት የማይመለስ ከሆነ “ቀጥቅጥ መዝራእቶ ለኃጥእ ወእለኩይ” ማለትም እጅእጁን መቀጥቀጥ ነው። በዚህም የማይመለስ ከሆነ፤ እራሱን ወደ ፍየል ለውጦ ከግራዝያን በተማረው ቴስታ እራስህን መትቶ እስኪያዞርህ ፋታ አትስጠው። ”ወቀጥቀጠ አርዕስቲሁ ለለይሲ“ ማለትም እንደ እባባ ራስራሱን በያዝከው ብትር ቀጥቅጠው ማለት ነው።

በዚህ ዘመን ያሉት ወያኔዎች በትግራይና በኦሮሞ መካከል የነበረውን እያየን ያደግነውን ቅጥቅጥ ማስወገዳቸው መልካም ቢሆንም፤ ከግራዝያን በለመዱት ቴስታ የሁሉንም ራስ ማዞራቸው የከፋ የሰይጣን ስራ ነው። በራሳቸው በወያኔዎችና በኦሮሞዎች መካከለ ብቻ የነበረውን ጥላቻ ነቅለው፤ በአማራና በኦሮሞ መካከል አድርገው፤ ኦሮሞውንና አማራውን ሆድና ጀርባ ካደረጉ በኋላ፤ እርስ በርሱ እንዲጠራጠር እንዲፈራራ፤ ከዚያም ባሻገር በአማራው ስም ኦሮሞውን በኦሮሞው ስም አማራውን ሲገድሉ ለ25 አመታት መቆየታቸው ታሪክ የማይረሳው ደባ ነው።

አባቶቻችን ከደመራው በዓል ስርአት ጋራ አያይዘው በማክበር የሚያስታውሱትን የ40ኛ ቁጥር ወያኔዎች ትርጉሟን ቀይረው ለአማራ ብቻ በመስጠት የተጠቀሙት ሰይጣናዊ ስራ ደግሞ ከሁሉም ይልቅ እጅግ የሚያስገርም ነው።

አባቶቻችን እንደነገሩን፤ 40 ዘመን ለ20 እና ለ60 እድሜ ማእከል ነው። በዚህ ዘመን ያሉ ሰዎች ለሀገር ልማትና ጥፋት ተጠያቂዎች ናቸው። ከ20 እስከ 60 ዘመን ላሉት ሰዎች ማእከል እድሜ 40 ዘመን ነው። ከ40 ዘመን ወደታች እስከ ከ 20 አመት ዕድሜ ያሉና፤ ከ40 ዘመን በላይ 20 አመት በመደመር እስከ 60 ዘመን ያሉ፤ በአካል በመንፈስ የበረቱ አቀበት በመውጣት ቁልቁለት በመውርድ ለአገር አጥር መከታ ለወገን ታዳጊና አለኝታዎች ናቸው። 40

ዘመን ማእከል አፍላ ናት። በዚህ ዘመን ያሉ ሁሉ በሀገር በወገን መከራ ሲመጣ ይጠራራሉ አንዱ ላንዱ ግራ ወይም ቀኝ እጅ በመሆን ከጠላት የሚወረወረውን መከታ በመሆን እየተረዳዱ የጋራ ጠላትን ያጠቁ ነበር።

”እናቴ ኢትዮጵያ ውለጅልኝ መንታ፤

ቀኝ እጇ ሲመከት ግራ እጇ ተመታ“

የሚለው የፈለቀው ከዚህ ነው። 40ኛ የሚለው ቃል ከረዥም ዘመን ዳህጸ ልሳን ወደ አርበኛ ተለወጠ። ይህ ታሪካዊ የኢትዮጵያዊነት አርማ ላንድ ላማራ ጎሳ ብቻ በመስጠትና ኦሮሞው ባማራ እንደተጠቃበት አድርገው በማቅረብ፤ በ40ኛነት አርማ ተሰልፈው ለአገር ለወገን መከታ የነበሩትን የኦሮሞዎችን አርባኞች እነ ራስ ራሱ ጎበናን፤ እነ ደጃች ባልቻን እነ ፍታውራሪ ሀብተ ጊርጊስን፤ በአ40ኛነታቸው ከሰሩት ታሪካዊ ክብራቸው አወጧቸው።

ከዚያም አልፈውና ተርፈው፤ በአጼ ምንይልክ ዘመን የነበሩት የጦር መሪዎች የኦሮሞ ልጆች እነ ራስ ጎበና ሲሆኑ፤ አማራውን ለማስጠላት ላደረጉት ማዳበሪያ የጡትን ቆራጭነት የጭካኔ ተግባር ለአጼ ምንይልክ ሰጡት። አጼ ምንይልክንም ለአማራው ወኪል አድርገው በሳቸው ላይ ያለበሱትን የጥላቻ ደበሎ አማራውን አለበሱት።

በዚህ ሁሉ ተንኮላቸው ኦሮሞና ኦሮሞ ምሰሶና ወጋግራ፤ አጥርና ግድግዳ ሆኖ ኢትዮጵያን የሰራ፤ በውስጡ ያሉትን ጎሳዎች የቀኝን የግራ ክንድ ሆነው መንከባከብ ሲጠብቁ እንዳልኖሩ ሁሉ፤ ዛሬ የባንዶች ልጆች በሸረቡት ሸፍጥ፤ አማራና ኦሮሞ ሌላውን ሊታደጉ ይቅርና እራሳቸውን መከላከል እንዳይችሉ አደረጓቸው።

በታላላቅ ጎሳዎች በአማራና በኦሮሞ ላይ ይህን ያህል ድፍረትና ትዕቢት እያሳዩ፤ ይህን ያህል ጭፍጭፋ ካደረሱ፤ በዳር አገር በሚኖሩት በቁጥራቸው አንስተኛ በሆኑት፤ ለምሳሌ አቶ ኃይለ ማርያም ደሳላኝ የበቀለበትን እንደ ወላይታ የመሳሰሉትን ጎሳዎች በከፋ ሁኔታ እንዳጠቋቸው መገመት ይቻላል። በነዚህ አንስተኛ ጎሳዎች ላይ የፈጸሙት ደባ እጅግ የሚከፋው ደግሞ፤ በኦሮሞውና ባማራው ላይ የፈለጉትን በደልና ግፍ ለመፈጸም ከመካከላቸው ያሉትን እንደ አቶ ኃይለ ማርያም ደሳላኝ የመሳሰሉትን መጠቀማቸው ነው።

ግራዝያን በኢትዮጵያ ውስጥ በቆየባቸው ባምስቱ አመታት በኢትዮጵያውያን ላይ የፈጸመው የተናጠልና የጅምል ጭፍጨፋ እንዳይረሳ ፤ የካቲት 16 ተብሎ በአራት ኪሎ ላይ ሀውልት ቆሟል። ከዚህ በመነሳት ስናስብ፤ ወያኔዎች የቆዩባቸው አመታት በ5 ተባዝተው 25 አመታት ናቸው።

ወያኔዎች በዚህ እጽፍ ድርብ ዘመናቸው በኢትዮጵያ ላይ የሚፈጽሙት መከራ፤ ግራዝያን ከፈጸመው መከራና ስቃይ ጋራ ሲነጻጸር መጠንና መስፈርት የለሽ ነው። በወልቃይት በጎንደር፤ በጎጃም፤ በባሌ፤ ባርሲ፤ በውጋዴን፤ በጋምቤላ፤ በኮንሶ፤ በወለጋና በሲዳሞ የፈጸሙባቸው ቦታዎች ሁሉ ተባዝቶ ሲደመሩ፤ የካቲት 16 ሀውልት ከሚያስታውሰን ግራዝያን ከፈጸመው ግፍና ጭካኔ እጅግ የከፋ ከ5 ጊዜ በላይ የከበደና የሚዘገንን ነው።

ወያኔ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረባት ቅጽበት ጀምሮ ብሩህ አዕምሮ ያላቸውን እያጠና እና እየመረጠ የፈጃቸው፤ ወላጅ ቤተሰብና መንደርተኛ ብቻ የሚያውቋቸው ዓለም የማያውቃቸው አሁን በጅምላ ከሚጨፈጭፋቸው በላይ ብዙ ናቸው። ወያኔዎችን ከአይሲሲም እጅግ የከፉ የሚያደርጋቸው፤ አይሲሶች እያረዱ የጣሏቸው ኢትዮጵያውያን በሰው አገር በሰው ባህር ነው፤ ወያኔዎች እያረዱ የጣሏቸው ግን፤ እየዋኙ ባደጉበት በጣና ባህር ነው።

ወያኔ በሚያፈሰው ደም ጥማቱን ባለማርካቱ፤ ደም ማፍሰሱን ለመቀጠል፤ ቤተ መንግስቱን ብለቅ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ረዋንዳ ህዝብ እርስ በርሱ ይጨራረሳል የሚል ሸፍጥ አያቀረበ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ እርስ በርሱ ተጨራረሰ፤ በራሱ በወያኔ ተጨረሰ ምንድነው ለውጡ?

የኢትዮጵያ ህዝብ ራሱን ለመምራት ምንም ልምድ እንደሌለው፤ ከጋርዮሽ ዘመን ገና እንዳልተላቀቀና ከረዋንዳ እንኳ መማር የማይችል እርስ በርሱ የሚተላለቅ አድርገው በማቅረባቸው፤ የኢትዮጵያውያንን የረዥም ዘመን ልምድና ስነ ምግባር መካድ የሚያስቆጣና የሚያበሳጭ ከሰይጣናዊ ተግባር እጅግ የከፋ ነው።

## የትግራይ ሽማግሎች ምሁራን አዛውንት ባልቴቶች ወገኖቻችን ሆይ ! ይታያችሁ !

የውጭ ወራሪዎች ሰርገው በገቡ ጊዜ ለአገራቸውና ላንድነታቸው ጸንተው የቆሙ ወያኔዎችን የታገሉት የትግራይ አርባኞች እነ ራስ አሉላ፤ ከኢትዮጵያውያን ጋራ ለነበራቸው አንድነትና ለመተማመናቸው ምልክት አርገው፤ የመጣበቅ ባሕርይ ያላትን ሐርግ፤በራሳቸው ላይ በመጠምጠም የተጠቀሙባትን በአማረኛ <u>አሽከት</u> በትግርኛ <u>ጸጎጎት</u> የምትባለውን አትርሱ።

ከወያኔወች ጋራ ተሰልፈው በአማራውና በኦሮሞው ደም ላይ ቆመው ወሮ ወሸባየ እያሉ ለሚዘፍኑት ለሚፎክሩት ለትግራይ ወጣቶች ይህንን ያንድነት ታሪክ ንገሩ። መስከረም <u>፲፯</u> በያመቱ <u>ጽንዒ</u> እያሉ የትግራይ ወገኖቻችን እንደሚያስታውሷት አትደብቁ !

በፌደራል በቅስና በምንኩስናና እና በጵጵስና ወያኔነትን ሰውራችሁ፤ በአማራውና በኦሮሞው ምድር ገብታችሁ፤ አይሲስ ለእርድ ሲነዳቸው እንደታዩት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች፤ እናንተም እስካሁን ከገደላችሁት የተረፈውን የአማራውንና የኦሮሞውን ወጣት ለእርድ መንዳታችሁን አቁሙ ! እያላችሁ ከቀረው ወገናችሁ ጋራ እንድትሰለፉ ሽምግልናችሁ ያስገድዳችኋል።

"አማራውም ኦሮሞውም ጋምቤላውም ኮንሶውም አፋሩም ኦጋዴውም ሰብሮ የወጣው እየተገደለ ነው፤ እናንተም እየተገደላችሁም ቢሆን ሰብራችሁ በመውጣት ከቀረው ኢትዮጵያዊው ወገናችህ ተቀላቀሉ" ብለው የተከበሩ አቶ ገብረ መድህን አርአያ የተናገሩትን ለሁሉም አዳርሱ። ይህን ብታደርጉ ራሳችሁን ከትውልድና ከታሪክ ተወቃሽነት ታድናላችሁ።

## <u>በዚህ ዘመን ከ20 እስከ ስድሳ እድሜ ያላችሁ</u>

"መላ ሰውነቴ ወደ ውህነት ተለውጦ ተደፋ። አጥንቴም ደቅቆ ወደ አፈር ትቢያነት ተለውጦ ተበታተነ። ልቤም እንደሰም ቀልጣ በአንጀቴ ፈሰሰች" (መዝሙር 22፡ ) በሚለው አፍአዊ ቃል ብቻ ሳንወሰን ከሚታገለው ወጣት ጋራ እንሰለፍ። በዚህ ዘመን ከ20 እስከ 60 እድሜ ላይ ያለ በዚህ በወያኔ ክፉ ዘመን የተጠራውና የካተተ 40ኛ ነው።

ፖርቹጋሎች በእርዳታ ስም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው አንወጣም ብለው ወረራቸውን በቀጠሉ ጊዜ፤ በትግራይና በመላ ኢትዮጵያ የነበሩት አ40ኞች "በወረሩን ሰዎች ለዘላለም እየተሰቃየን ከመኖርና ለልጆቻችንም የተገዥነትን ውርስ ከማውረስ ከየቤታችን የጫርናት ይሕች የደመራ እሳት ትብላቸው" ብለው በደመራዋ እሳት ነጻ እንደወጡ፤ በዘመናችንም አማራው ኦሮሞው አፋሩ ጋምቤላውና ኮንሶው መሬቱን ከወረሩት ወያኔዎች ነጻ ለመውጣት የሚያደርጉትን ትግል ቆመን መመልከት እርም መብላት ነውና አቅማችን በፈቀደልን ሁሉ አብረን እንቁም !

በዓለም ዙሪያ የተበትን በውስጥም ያለን ክርስቲያኖች ሆይ ! በደረሰው ግፍ ተበሳጭተው በነ አቡነ ማትያስ ላይ የተማረሩት ካህናትና መነኮሳት በወሰዱት አቋም በዚህች ቅጽበት በመሰቃየት ላይ ካለው ወጣት ጋራ እንደሚያልቁና በመሰቃየት እንዳሉ የታወቀ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን ጵጵስናን ከተቀበለችበት ከፍሬምናጦስ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ በተፈራረቀባት የመከራ ዘመን ደማቸውን የቀላቀሉት ጳጳሳት ሁለት ብቻ ናቸው።

በዚህ አጋጣሚ በዘመናችን የተፈጸመውን ቀዳማዊ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴንና አቡነ ቴዎፍሎስ ያደረጉትን ሳናወሳ ማለፍ የለብንም።

"ኢትዮጵያ ትቅደም ያለምንም ደም" ብለው የተነሱት ደርጎች፤ ቀዳማዊ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴን ከዙፋኑ ይውረዱ ሲሏቸው፤ "እኛ እስካሁን አቅማችንና ጊዜያችን በፈቀደልን አገልግለናል ለህዝቡ አንድነትና ለድንበር ተጠንቀቁ" ብለው ምክር በመስጠትና፤ በዙሪያቸው ለነበሩት ምንስቴሮቻቸው ለጦር ኃይል አዛዦች አትቃወሙ እጃችሁን ስጡ እያሉ ተባብረዋል።

ደርግ የተባበሯቸውን ንጉሡን በመግደሉ፤ የጃንሆይን ምክር ሰምተው እጃቸውን የሰጡትን ሁሉ ወገኖች በመፍጀቱ፤ "ኢትዮጵያ ትቅደም ብላችሁ አታላችሁ፤ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠራችሁ በኋላ፤ ይህን ግፍ በመፈጸማችሁ፤ የምታደርጉትንና የምትናገሩትን ሁሉ ቤተ ክርስቲያን አትቀበላችሁም በማለታቸው" ደርጎች አቡነ ቴዎፍሎስን አንቀውና አሰቃይተው ገደሏቸው። በጣሊያን ከተገደሉት ከሁሉት ከአቡኑ ጴጥሮስና እና ከአቡነ ሚካኤል ጋራ ደማቸው ከህዝብ ደም ጋራ ተቀላቅሎ ሕይወታቸው ያለፈው፤ ከአቡነ ቴዎፍሎስ ጋራ ሶስት ብቻ ናቸው።

ዛሬም በዚህ ዘመን በጎንደርና በጎጃም ያሉት ጳጳሳት አንዲት ቃል ሳያሰሙ፤ በወያኔ ከሚጨፈጨፈው ወገናችሁ ጋራ በመሰለፍ በአቡነ ማትያስ የሚመራውን ሲኖዶስ አንቀበልም ማለታቸው ከዚህ ቀደም ሊቃውንት አበው የፈጸሙትን ታሪክ ደገሙት።

"ትኩን ደምየ ተፍጻሜ ደመ ኩሎሙ ሰማእታተ አንጾኪያ" ብሎ ጴጥሮስ ለአንጾኪያ ደም መፍሰስ መደምደሚያ ትሁን ብሎ የራሱን ደም እንዳቀረባት፤ በወያኔ ተጨፍጭፎ ከሚፈሰው ከወጣቱ ደም ጋራ ደማቸውን ተቀላቅሎ እንዲፈስ ራሳቸውን ለሰጡ በጎንደርና በጎጃም ላሉ ካህናት መነኮሳት ክብር ይገባቸዋል።

በደረሰብን መከራ ውሀ የሆነውን ሰውነታችንን፤ የደቀቀውን አጥንታችንን፤ የተሰበረውን ልባችን እግዚአብሔር ይጠግንልን ፤ የተናወጠችውን ኢትዮጵያን ወደ ቀደመ ከብሯ ይመልስልን ዘንድ፤ ተግባር ባልተለየው ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት እንድንቆም